# የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን

## የ1997 የሰው ኃይል ጥናት የመጠይቅ ዕርማትና ኮድ አሰጣጥ መመሪያ

**(Editing and Coding Manual)**

ሚያዝያ 1997
አዲስ አበባ

# የ1997 የሰው ኃይል ጥናት የመጠይቅ ዕርማትና ኮድ አሰጣጥ መመሪያ

## (Editing and Coding Manual)

## I. መግቢያ

የሰው ኃይል ስታትስቲክስ መረጃዎች ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የልማት ዕቅዶችን ለመንደፍ፣ ስለአፈፃፀማቸው ለመከታተልና አስፈላጊ እርምጃዎችን ለመውሰድ መሠረታዊ በመሆናቸው በየወቅቱ መረጃዎች በመስኩ እንዲሰበሰቡ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሠረት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን በመጋቢት 1997 አገር አቀፍ የሰው ኃይል ጥናት በማድረግ መረጃ ሰብስቧል፡፡ ጥናቱ ግቡን እንዲመታ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉት ስራዎች መካከል አንደኛው ከመስክ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በሚገባ አርሞና ኮድ ሰጥቶ ለሚቀጥለው የሥራ ክፍል ማስተላለፍ ነው፡፡ ስለሆነም የኮድ አሰጣጥና ዕርማት የማድረግ ተግባር በጥንቃቄ መከናወን ይኖርበታል፡፡ በተለይም በዚህ ጥናት ከተካተቱት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጥያቄዎች፣ እነዚህንም ጥያቄዎች እርስ በርስ ለማመሳከር ከሚፈጥረው ውስብስብ አሠራር አኳያ አራሚው የጥናቱ የመረጃ አሰባሰብ በቂ ዕውቀት ሊኖረው ይገባል፡፡ በተጨማሪ የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም የአገልግሎት መረጃ ኮድ ሲደረግ በመጠይቁ የተሞሉትን መረጃዎች በጥሞናና በእርጋታ ማየትና መረዳትን ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም በመጠይቁ እርማትና ኮድ መስጠት ሥራ የሚሳተፉ ሠራተኞች የጥናቱን ውጤት በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ የሥራ ድረሻ የተጣለባቸው መሆኑን አውቀው የእርማትና ኮድ አሰጣጡን መመሪያ በደንብ መረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## II. አጠቃላይ መመሪያ

### ሀ. ኤዲቲንግ፡

ከልዩ ልዩ ጥናቶች የሚሰበሰቡትን መረጃዎች ኤዲት ማድረግ /ማረም/ የመረጃውን ጥራት ለመገምገምና እንደዚሁም ስህተቶችን፣ የሚቃረኑ መረጃዎችን፣ ሳይሞሉ የቀሩትን፣ ...ወዘተ በማረም የመረጃውን ጥራት ለማሻሻል ይረዳል፡፡

ኤዲቲንግ ማለት የተሰበሰበውን መረጃ ሁኔታ በመመልከት በተሰጠው መመሪያ መሠረት አስፈላጊውን እርማት ማድረግ ነው፡፡ ኤዲተሩ /አራሚው/ ይህንን ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት የመረጃ መሰብሰቢያው ፎርም /መጠይቅ/ ለመረጃ ሰብሳቢው በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት መሞላቱን ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡ ኤዲተሩ /አራሚው/ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 1. ሳይሞሉ የቀሩ መረጃዎች

በመጠይቁ ሳይሞሉ የቀሩትን መረጃዎች በመፈለግ መመሪያውን በመከተል አስፈላጊውን እርማት ማድረግ ነው፡፡ ሣይሞሉ በቀሩ መረጃዎች ፋንታ የሚሞላው መረጃ የሚገኘው ሌሎች የተሞሉ መረጃዎችን በማገናዘብና በመመርመር ነው፡፡ በተቻለ መጠን ለተዘለሉና ሣይሞሉ ለቀሩ መረጃዎች በሙሉ አስፈላጊው እርማት ተደርጐ መሙላት የሚያስፈልግ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም ሣይሞሉ ለቀሩት መረጃዎች በፎርሙ /መጠይቁ/ ከታዩት መረጃዎች አኳያ አመሳክሮና መርምሮ ለማረም የማይቻል ከሆነ በፈጠራ መሙላት ስለማይገባ ሣያርሙ ዓምዱን ባዶውን መተው ይመረጣል፡፡ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ኮድ ሲደረግ ላልታወቀ መልስ የሚሰጠው ኮድ ይሰጠዋል ማለት ነው፡፡

## 2. ሊሆኑ የማይችሉና የማይመስሉ መልሶች

ሊሆኑ የማይችሉ መልሶችና የማይመስሉ መልሶችን በእርማት ጊዜ ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ ሊሆኑ የማይችሉ መልሶች በመመሪያው ከተሰጠው ውጭ የተመለሱ መልሶች ሲሆኑ ለምሳሌ፣ ባለፈው ሳምንት ለስንት ቀናት ሠሩ? የሚል ጥያቄ ቢኖርና በዓምዱ የሰፈረው ቀናት ብዛት ከ7 ቀን በላይ ከሆነ ይህ ሊሆን የማይችል መልስ በመሆኑ መታረም አለበት፡፡ የማይመስሉ መልሶችን በተመለከተ የጋብቻ ሁኔታን እንደ ምሣሌ ብንወስድ የአንድ ሰው የጋብቻ ሁኔታ፣

1/ ፈጽሞ ያላገባ/ያላገባች
2/ ያገባ/ያገባች
3/ ባል/ሚስት የሞተባት/የሞተችበት
4/ የተፋታ/የተፋታች
5/ የተለያዩ

ሲሆን ይህም መረጃ የሚሞላው ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ለቤተሰብ አባላት በሙሉ ነው፡፡ ለአንድ ዕድሜው 11 ዓመት ለሆነ ልጅ የጋብቻ ሁኔታ "ሚስት የሞተችበት" ተብሎ ቢሞላ በዚህ ዕድሜው አግብቶ ሚስቱ ልትሞትበት ስለማይችል መልስ ሊሆን የማይችል በመሆኑ መታረም አለበት፡፡ እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ መልሶች ተመዝግበው ሲገኙ ከቀሩት ዓምዶች ጋር በማገናዘብ መረጃው ይታረማል፡፡

3. የ<u>ሚቃረኑ መልሶች </u>በተለያየ ዓምድ ላይ የተሞሉ መረጃዎች ለምሳሌ በዓምድ 20 እና 21 ላይ ስለትምህርት የተሞላው መረጃ መልስ ሰጪው በአዲሱ የትምህርት ሥርዓት 10ኛ ክፍልን እንዲሁም በቀድሞ 12ኛን እንኳ ያልጨረሰ ቢሆንና በዓምድ 23 ላይ የስልጠናው ዓይነት ኘሮፌሽናል ቢሆን የሚቃረኑ ስለሆኑ ማረም ተገቢ ነው፡፡ የሚቃረኑ መልሶች የሚባሉት ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ መልሶች ሳይዛመዱ ሲቀሩ ነው፡፡

## 4 ጽሁፉን ለማንበብ የሚያስቸግሩ መልሶች

በትክክልና በደንብ የማይነበቡ መልሶችን ማረምና ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም እርማቱ በሚደረግበት ወቅት የሚፃፉ ጽሁፎች ሁሉ በደንብና በቀላሉ የሚነበቡ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## 5. <u>ከመመሪያ ውጭ ስለተሞሉ መልሶች /የይለፍ ትዕዛዞች ካልተከበሩ/</u>

ለምሳሌ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ሥራ ሠርተዋል? ተብለው ለተጠየቁት መልስ "የለም" ብለው ኮድ "2" ለተሞላላቸው በሚቀጥለው ዓምድ የሥራ ሰዓት ተሞልቶ ከተገኘ የነዚህ ዓምዶች መልስ የሚቃረኑ መልሶች ናቸው፡፡ ይህም ማለት በሳምንት ውስጥ ምንም ሥራ ያልሰራን ሰው ስንት የሥራ ሰዓቶች ሠራህ ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ነገር ግን በመጀመሪያው ዓምድ ላይ የተሞላው ኮድ "2" የለም የሚለውን ስህተት ሊሆን ስለሚችል ተከታታይ ዓምዶችን መርምሮ ማየት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በዚህ ጥናት ከመመሪያ ውጭ የተሞሉ መረጃዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ የስልጠናና የጋብቻ ሁኔታ የሚጠየቀው ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ዕድሜው 9 ዓመት ለሆነው ህፃን የስልጠናና የጋብቻ ሁኔታ ተሞልቶለት ቢገኝ ምንም እንኳ ዕድሜያቸው 9 ዓመትና በታች የሆኑ ህፃናት መመሪያው ዕድሜያቸው 10 ዓመት እስካልሞላ ድረስ ስለስልጠና ጋብቻ ሁኔታ የሚያመለክቱ መረጃዎች እንደማይጠበቅባቸው ስለሚገልጽ የተሞላው መረጃ ከመመሪያ ውጭ ስለሆነ መሠረዝ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የዓምዶችን ቅደም ተከተል ለማመልከት መረጃዎች ሲሞሉ ከየትኛው ዓምድ ወደ የትኛው ማለፍ እንደሚገባ በመጠይቁ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ስለሆነም መረጃዎች ይህንኑ ተከትለው መሞላት ስለሚገባቸው በመጠይቁ ላይ በተመለከተው መሠረት ያልተሞሉ መረጃዎች ከተገኙ መታረም ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ በዓምድ 14 እድሜው ከ 10 ዓመት በታች የተሞላለት ሰው ከዓምድ 20 እስከ ዓምድ 27 ያሉት ጥያቄዎች በሠረዝ መታለፍ ይኖርባቸዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ዓምዶች ተሞልተው ከተገኙ ሌሎች ዓምዶችን በማገናዘብ ማስተካከልና ማረም ያስፈልጋል፡፡

## 6. በጽሑፍ የተሰጠ መልስና ኮድ አለመጣጣም

በመጠይቁና በመመሪያው ውስጥ በግልጽ እንደተመለከተው ለአሠራር ያመች ዘንድ መረጃዎች በኮድ ብቻ (ከጥቂት ዓምዶች በስተቀር) እንዲገለጽ ተደርጓል፡፡ሆኖም አንዳንድ መረጃ ሰብሳቢዎች በስህተት መልሶቹን በቃላትና በኮድ ሊመዘግቡ ይችላሉ፡፡ ይህ አሠራር በተለይ መረጃዎች በኮምፒውተር በሚቀነባበሩበት ወቅት ችግር ስለሚፈጥሩ በቃላት የተመዘገቡትን መረጃዎች ከሚጣጣመው ኮድ ጋር ተገናዝቦ መሞላት ይገባዋል፡፡ስለዚህ በጽሑፍና በኮድ የተሰጠው መልስ ሲለያይ ሌሎች ተዛማጅ ዓምዶችን መመልከት ተገቢውን እርማት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## ለ. <u>ኮዲንግ፡-</u>

ኮዲንግ ማለት በፎርሙ የተሰጡትን መልሶች ወደ አሀዝ መለወጥ ነው፡፡ ይህም አሀዝ በቀላሉ መረጃውን በኮምፒውተር ለማቀነባበር ይረዳል፡፡ የእርማትና (Editing) የኮድ የማድረግ ተግባር በማጣመር ይካሄዳል፡፡ በዚህ ፎርም የተሞሉት መረጃዎች በአብዛኛው አስቀድመው ኮድ ተደርገዋል፡፡ <u>ለምሳሌ</u> ጾታ፣ ዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ...ወዘተ ናቸው፡፡ ለነዚህ መልሶች የእርማት ተግባር ለማከናወን ኮዶቹ በመመሪያው መሠረት መሞላታቸውን ማረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ እንደ አዲስ ኮድ መደረግ ያለባቸው መልሶች ደግሞ በክፍል 1 የተገለፁት የአካባቢ መለያ መልሶች

ናቸው፡፡  እነዚህን መልሶች ኮድ ለማድረግ የሚረዱ የኮድ ዝርዝር ይሰጣል፡፡  ይህ የኤዲቲንግ ኮዲንግ መመሪያም የአሠራሩን ሁኔታና ዘዴ የሚገልጽ ጽሁፍ ነው፡፡

- የእርማቱና ኮድ አሰጣጡ ሥራ መከናወን ያለበት ለዚሁ በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት መሆን እንዳለበት ማስታወስ ይገባል፡፡ አንዳንድ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያልተጠቀሱ ነገሮች ሲያጋጥሙ ጥያቄዎቹን ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማቅረብ መፍትሔ እንዲሰጠው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- ሥራውን ለማከናወን መነሻው በመስክ የተሞላው መረጃ ስለሆነ አስቀድሞ እያንዳንዱ መጠይቅ መሞላቱንና ተሟልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በአንድ ቆጠራ ቦታ ለ30 ቤተሰቦች መረጃ ተሞልቶአል፡፡ ለእያንዳንዱ ቤተሰብም አንድ ባለ 5 ገጽ /A3 Size/ መጠይቅ የተሞላ ሲሆን፣ ተጨማሪ መጠይቅም ተሞልቶላቸው ከሆነ ሁለት ባለ 5 ገጽ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ አንዳንድ በመረጃው አሰባሰብ ጊዜ ያጋጠሙትን ሁኔታዎች የሚያብራሩና ከመጠይቁ ጋር ተያይዘው የመጡ አስተያየቶችን በሚገባ መያያዛቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

- እርማት በሚደረግበትና ኮድ በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉ ሥራው ከሚመለከተው ኃላፊ ካልታዘዘ በስተቀር ማንኛውም በመረጃ ሰብሳቢው የሰፈረው ነገር መፋቅ/መጥፋት የለበትም፡፡ መረጃውን እርማት የሚያደርግበት ከሆነ ካሰፈረው መረጃ አጠገብ መረጃው ከተፃፈበት ቀለም በተለየ ቀለም እርማቱ ይደረጋል፡፡

# III መጠይቆችን ማረም

## ክፍል 1፡- የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ

ከዓምድ1 እስከ ዓምድ 8 ያለውን የክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ከፍተኛ/ወረዳ/ ቀበሌ ስሞች በመጠይቁ ሽፋን ገጽ ላይ እና በየመጠይቆቹ አናት ላይ ተሞልተዋል፡፡ እነኚህ ከክልል እስከ ቀበሌ ላሉት ዓምዶች ካርድ ኮለሞቹ መስክ ላይ የተሞሉ ስለሆነ፣ በተለይ ተዘጋጅቶ የቀረበውን የአካባቢ መለያ ኮድ መጽሐፍ በመጠቀም ካርድ ኮለሞቹ በትክክል ተሞልተው መምጣታቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የቆጠራ ቦታ ኮድ በትክክል መሠጠቱን ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ጥናቱ የተካሄደበት የቅ/ጽ/ቤት ስምና ኮድ ካርድ ኮለም መሞላት አለባቸው፡፡ ተጨማሪ መጠይቅ መኖሩ አለመኖሩ በተከታይ ዓምድ በማየት ማረጋገጥ ይሆናል፡፡

ዓምድ 1-3 ፡- ክልል፣ዞን፣ወረዳ፡- ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል፣ዞንና ወረዳ ስም በዓምዱ በተሰጠው ቦታ በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ዓምድ 4 ፡ -ከተማ፡ -ከከተማው ጥናት የተመረጠው የከተማ ስም በተሰጠው ቦታ በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ኮዱ ደግሞ በካርድ ኮለሞች ይሞላል፡፡ በካርድ ኮለሞቹ /Area Code Book/ ተስማሚው ኮድ መስጠቱ ይረጋገጣል፡፡

ዓምድ 5፡ -ከፍተኛ/ ወረዳ/፡ - ጥናቱ በከተማ የተካሄደ ስለሆነ የከፍተኛው/የወረዳው ስም ፣በዓምዱ በተሰጠው ቦታ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ 6፡ - ቀበሌ፡ - በከተማው ውስጥ ቀበሌው የሚጠራበት ስም/ቁጥር በተሰጠው ቦታ መሞላቱን ማረጋገጥ እና በካርድ ኮለሞቹ ደግሞ የቀበሌው ኮድ ከአካባቢው መለያ ኮድ በመጠቀም በካርድ ኮለሞቹ /Area Code Book/ ተስማሚው ኮድ መስጠቱ ይረጋገጣል፡፡፡፡

ዓምድ 7፡ -የቆጠራ ቦታ፡-የቆጠራ ቦታ ኮድ በካርድ ኮለሞቹ በትክክል መሞላቱን ማጤን ያስፈልጋል፡፡ ለከተማ የቆ.ቦታ በሦስት ዲጂት /Digit/ መሞላቱን ማየት ያስፈልጋል፡፡ በገጠር ግን በሁለት digit መሆኑን ማየት ያሻል፡፡

ዓምድ 8፡ - የተመረጠው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር፡- በአንድ የቆጠራ ቦታ በጥናቱ የሚመረጡ ቤተሰቦች በጠቅላላ ብዛት 30 ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ዓምድ ባሉት በካርድ ኮለም የተሞሉት ቁጥሮች ከ01 -30 መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ8ሀ፡- የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም ፡ - በዚህ ዓምድ የቤተሰቡ ኃላፊ ሙሉ ስም መፃፉን እንዲሁም በክፍል 2 ዓምድ 11 በመጀመሪያ ተራ ቁጥር ላይ መመዝገቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ባይሆን ግን ከተቆጣጣሪው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ 9ሀ፡- ቅ/ጽ/ቤት
በዚህ ዓምድ የቅ/ጽ/ቤቱ ሥም በዓምዱ በተሰጠው ቦታ ተሞልቶ ለቅ/ጽ/ቤቱ የተሰጠው መለያ ኮድ ደግሞ ከዓምዱ ሥር ባሉት ሁለት ካርድ ኮለሞች ይሞላል፡፡

ዓምድ 9ለ፡-የቆጠራ ቦታ ተከታታይ ተራ ቁጥር

ከተዘጋጀው ኮድ መጽሐፍ /Code Book/ ለዚህ ቆጠራ ቦታ የተዘጋጀው ኮድ በሁለቱ ካርድ ኮለሞች ይሞላል፡፡

ዓምድ 9ሐ፡- የቀጠለ መጠይቅ አለ?

ከተሞላው መጠይቅ በተጨማሪ የቀጠለ ወይም የተጨመረ መጠይቅ መኖሩንና አለመኖሩን የሚረጋገጥበት ስለሆነ መጠይቁ ታርሞ ከማለቁ በፊት በጥንቃቄ መታየት ይኖርበታል፡፡ የተሞላውን ኮድ ምልክት መሠረት በማድረግ የቀጠለ አለመኖሩን ማጣራትና ተገቢውን እርማት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ የቀጠለ መጠይቅ ካለ ከዋናው መጠይቅ ጋር በስቴፕለር መያያዝ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል 2፡ ስለቤተሰብ አባላት ዝርዝር መረጃ

## ከዓምድ 10-19A ለሁሉም የቤተሰብ አባላት የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**ዓምድ 10፡-** ተራ ቁጥር፡- ይህ ከ01 በመጀመር በተከታታይ ቁጥር የተሰጠበት ስለሆነ ምንም አይነካም፡፡ ሆኖም የቤተሰቡ አባላት ከ11 በላይ በመሆናቸው በተጨማሪነት ጥቅም ላይ የዋለ መጠይቅ መሆነ ከተረጋገጠ እና ተራ ቁጥሮቹ በመስክ ላይ ካልተስተካከሉ አራሚው በተጨማሪ መጠይቅ ላይ «01 » ወደ «12»፣ «02» ወደ «13» በመቀየር ማረም ይኖርበታል፡፡

**ዓምድ 11፡-** የቤተሰብ መደበኛ አባላት ሙሉ ስም፡-

የቤተሰቡ አባላት ስም የሰፈረበት ዓምድ ስለሆነ ምንም ዓይነት እርማት አይደረግበትም፡፡

**ዓምድ 12፡-** ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና፡- በዚህ ዓምድ ሥር ባለው ንዑስ ዓምድ መረጃ ሰብሳቢው መሙላት ያለበት የኮድ ቁጥሮች ከ0-8 ያሉ ብቻ ናቸው፡፡ አባላቱ ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸውን ዝምድና የሚገልጽበት ኮዶች እና የተሰጠው መግለጫና ኮድ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ እና የማይዛመድ ከሆነ ኮዱን ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ የኮዶቹ ዝርዝርና መግለጫቸው ከጥያቄው ሥር ይገኛል፡፡

**ዓምድ 13፡-** ጾታ፡- በዚህ ዓምድ ባለው ክፍት ቦታ መታየት ያለባቸው 1 ወይም 2 ብቻ ናቸው፡፡ ስለ ኮዱ ትክክለኛነት በዓምዱ ሥር በተሰጠው ቦታ የሰፈረውን የጾታ መለያ ማየት ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም መረጃ ሰብሳቢው በስህተት ኮድ ሳይሰጥ ቢቀር ተቆጣጣሪውን በማማከር የግለሰቡን ጾታ ከልዩ ልዩ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ መሞላት ይኖርበታል፡፡ ኮድ 9 አይፈቀድም ፆታ ካልተፃፈ ስም ታይቶ ይሞላል፡፡

**ዓምድ 14፡-** ዕድሜ፡- ይህ ዓምድ መስክ ላይ ተሞልቶ የሚመጣ ነው፡፡ ሆኖም በዚህ ዓምድ ባሉት ንዑስ ዓምዶች ከ97 በላይ ቁጥር መታየት የለበትም ከ97 በላይ የሆነ ቁጥር ከታየ 97 ተብሎ መስተካከል ይኖርበታል፡፡ ኮድ 99 አይፈቀድም ዕድሜ ካልተፃፈ ዝምድናና የልጆች ዕድሜ፣ የባል ዕድሜ ታይቶ በግምት ይሞላል፡፡ በተጨማሪም የዕድሜ መረጃ ካልተሞላ የቤተሰብ አመዘጋገብ ቅደምተከተልና በዕድሜ ከተገደቡ ዓምዶች ለግለሰቡ የተሞሉ መረጃዎችን በማመሳከር መረጃውን ለመሙላት ይሞክር፡፡ ይኸውም ሲሆን ከተቆጣጣሪው ጋር በመማከር የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## ከዓምድ 15-18፡- የፍልሰት ሁኔታ

**ዓምድ 15፡-** እዚህ ወረዳ ገጠር/ከተማ ውስጥ ያለማቋረጥ ስንት ዓመት ኖረዋል?

ይህ ዓምድ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል አሁን በሚገኝበት ወረዳ ገጠር/ከተማ ውስጥ ያለማቋረጥ ለስንት ዓመት እንደኖረ የሚጠይቅበት ነው፡፡ ለዚህም የተለያዩ አማራጮች ከኮድ 0-8 ከጥያቄው ሥር ተዘርዝረዋል፡፡

ስለሆነም በዚህ ዓምድ ውስጥ በሚገኘው ንዑስ ዓምድ የሚሞላው ቁጥር ከ0-8 ካሉት ቁጥሮች ውጭመሆን የለበትም፡፡ በተጨማሪም ከተወለዱ ጀምሮ አሁን በሚገኙበት ወረዳ ገጠር/ከተማ ላሉ ማለትም ኮድ8 ለተሞ ላሳቸው እና ከ5 ዓመት በፊት አሁን ወደ ሚገኙበት ከተማ/ወረዳ ለመጡ (ከኮድ 5-7 ለተሞላላቸው ) ከዓ ምድ 16-18 ምንም ሳይሞላ በሰረዝ መታለፉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ዓምድ ሳይሞላ ከመጣ የሚቀጥለ -ት ዓምዶችን በማየት ወይም ከዕድሜ (በተለይ ለህፃናት) ጋር በማገናዘብ ለመሙላት መሞከር ያስፈልጋል፡፡ ተቆጣጣሪውም ይህን ማየት አለበት፡፡

## ዓምድ 16-18፡- ለፈለሱ (በዓምድ 15 ከኮድ 0-4 ለተሞላላቸው)

### ዓምድ 16፡- እዚህ ወረዳ ገጠር/ከተማ ከመምጣትዎ በፊት የትኛው ዞን ነዋሪ ነበሩ?

በዓምድ 16 ውስጥ የተገለፀው የዞን ስም የተሰጠውም ኮድ ትክክል መሆኑ ይጣራ፡፡ የዞን ስምና ኮዱ አንድ መሆናቸውን ለማመሳከር በዚህ መመሪያ ዕዝል 4 የተሰጡትን የኮድ ዝርዝሮች ይመልከቱ፡፡

### ዓምድ 17፡-እዚህ ወረዳ ገጠር/ከተማ ከመምጣትዎ በፊት ቀድሞ ይኖሩበት የነበረው ሥፍራ ከተማ ነበር ወይስ ገጠር?

በዚህ ዓምድ ሥር የሚሰፍረው የከተማ ስም ወይም «ገጠር» የሚለው ቃል ነው፡፡ በካርድ ኮለሙም ውስጥ መገኘት ያለበት ኮድ 1-3 ወይም ኮድ 4 ብቻ ነው ፡፡ ነገር ግን ከላይ ከተገለጸው ውጭ ለከተማ የከተማው ስም መጻፍ ሲኖርበት «ከተማ» ተብሎ ከመጣ ስህተት ሊሆን ስለሚችል ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ ማሳወቅ ይገባል፡፡ በተጨማሪም እንደየከተማው ሕዝብ ብዛት ትንሽ፣ መካከለኛና ትልቅ ከተማ ተብሎ የተከፈለ ሲሆን፣ ይኸው ኮድ ከተዘረዘሩት ከተሞች ጋር መጣጣሙን ማየት ያስፈልጋል፡፡ ለከተማ ከኮድ 1-3 ለገጠር ደግሞ ኮድ 4 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በዞኖች ሥር የሚገኙ ከተሞች ዝርዝር ከዚህ መመሪያ ዕዝል 4ና በማኑዋሉ ውስጥ ገጽ26 የቀረበ ስለሆነ በዓምዱ የተፃፈው የከተማ ስም ዝርዝር መሠረት ተመሳክሮ ትክክለኛነቱ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

### ዓምድ 18፡ የቀድሞ መኖሪያዎን ለመልቀቅ ያበቃዎት ምክንያት ምንድነው?

ይህ ዓምድ በዓምድ 15 ላይ ፈልሰው ማለትም ከኮድ 0-4 ካሉት ኮዶች አንዱ ለተሞላላቸው ግለሰቦች በምን ምክንያት እንደፈለሱ/የቀድሞ መኖሪያቸውን እንደለቀቁ/ ተጠይቆ ምክንያቱ እና ከሥር በሚገኘው ካርድኮ ለም ደግሞ ተስማሚው ኮድ የተሞላበት ዓምድ ነው፡፡ በካርድ ኮለሙም የሚሞሉት ቁጥሮች ከ01-12 ያሉት ብቻ መሆን አለባቸው፡፡ በዚህ ዓምድ በካርድ ኮለሙ ኮድ 12 ተሞልቶ የሰጡት ምክንያት በዓምዱ ከተመዘ ገበ ይህን የተሞላ ምክንያት በትኩረት በመመርመር ከጥያቄው ሥር ከ01-11 ከተዘረዘሩት መልሶች ጋር የሚመሳሰል ከሆነ ከካርድ ኮለሙ ኮድ 12ን በመሰረዝ ተቀራራቢውን ኮድ መሙላት ያስፈልጋል፡፡

## ዓምድ 19-19A የአካል ጉዳት ሁኔታ

በዚህ ዓምድ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የአእምሮ/የአካል ጉዳት እንዳለበት አንድ በአንድ የበሽታወ ጉዳት ዓይነት ተዘርዝሮ የተጠየቀ ሲሆን፣ ለጥያቄውም ኮድ 1 ወይም 2 ብቻ መሞላቱን ማየት የሚያስፈልግ ሲሆን፣ ኮድ 2 የተሞላላቸው ደግሞ ወደ ዓምድ 20 ተላልፈው መጠየቃቸውን ማየት ይገባል፡፡

ዓምድ 19

(ስም) የማየት ችግር አለባቸው?

(ስም) የመስማት ችግር አለባቸው?

(ስም) የአእምሮ ዝግምተኛነት አለባቸው?

(ስም) የመናገር ችግር አለባቸው?

(ስም) የመቆም/የመራመድ ችግር አለባቸው?

(ስም) የሰውነት አካል አለመንቀሳቀስ ችግር አለባቸው?

((ስም) የአእምሮ መታወክ አለባቸው?

(ስም) ሌላ የአካል ጉዳት/የአእምሮ ችግር አለባቸው?

**ዓምድ 19A. የጉዳቱ ዓይነት ምንድነው?**

በዚህ ዓምድ መረጃ የተሞላላቸው ግለሰቦች በዓምድ 19 ለይ ተጠይቀውና የአካል ወይም የአእምሮ ችግር አለባቸው የተባሉ ናቸው:: ይህ ዓምድ ደግሞ ለማጣሪያው ዓምድ /ዓ.19/ ላይ አዎን ብለው ኮድ "1" የተሞላላቸው ሲሆን፣ ለዚህም ዓምድ ከተሰጡት 11 አማራጮች መካከል አንዱ ተሞልቷል:: ስለሆነም፣ አንዳንድ የጉዳት ዓይነቶች ተብለው የሚፃፉ <u>በሽታዎች</u> ሊሆኑ ስለሚችል ምንም እንኳን ኮድ 11 ተሰጥቶ የተገለፀ ቢሆንም ሁኔታውን በመመርመር የሚስተካከሉበትን መንገድ መፈለግ ያሻል:: በሌላ መልኩ ደግሞ ሁለት፣ሦስት ዓይነት ጉዳት ያጋጠማቸው ሰዎች ከተገኙ ሁሉም የአደጋ ዓይነት በጣምራነት ባይኖርም ከተጠቀሱት የጉዳት ዓይነቶች ውስጥ ካለ እርሱን አማራጭ የያዘው ኮድ ይሰጠዋል::

<u>ዓምድ 20-21:</u>- <u>የትምህርት ሁኔታ (ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆኑ ብቻ)</u>

እነኒህ ዓምዶች የሚሞሉት ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ ስለሆነ ከ5 ዓመት በታች ለሆነ ልጅ መረጃ ተሞልቶ ከመጣ ስህተት ስለሆነ ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ በማሳወቅ መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል:: በአንፃሩም ከ5 ዓመት በላይ የሆነ ግለሰብ መረጃ ሳይሞላለት ከመጣ ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳ የት ተገቢውን ኮድ መሙላት ተገቢ ነው::

<u>ዓምድ 20:</u>- <u>ማንበብና መጻፍ ይችላሉ ?</u>

ይህ ዓምድ 5 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰቡ አባላት ማንበብና መጻፍ መቻላቸው ተጠይቆ «አዎን» ለ መለሱ ኮድ 1 «የለም» ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 የተሞላበት ነው:: ስለዚህ በካርድ ኮለሙ ውስጥ ተሞልተው የሚመጡት ቁጥሮች ከ1 ወይም ከ2 ውጭ መሆን የለባቸውም:: ይህ ዓምድ ሳይሞላ ከመጣ በሚቀጥለው ዓ ምድ (ዓምድ 21) ላይ ከተሞላው መረጃ በመነሳት ማስተካከል ስለሚቻል ኦዲተሩ ለተቆጣጣሪው ማግከር አ ለበት::

## ዓምድ 21፡ የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ስንተኛ ነው?

በመጀመሪያ በዚህ ዓምድ መረጃ የሚሞላው በዓምድ 20 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ማለትም ማንበብና መጻፍ ለ ሚችሉ ግለሰቦች ብቻ ስለሆነ በዓምድ 20 ኮድ 2 ለተሞላላቸው በዚህ ዓምድ ምንም ዓይነት መረጃ እንዳልተ ሞላ ማረጋገጥ ተሞልቶም ከመጣ ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ ጋር በመመካከር መረጃውን መሰረዝ እንደሚያስ ፈልግ መገንዘብ ያስፈልጋል። ቀጥሎም ከላይ ባለው ሰፋ ባለ ክፍት ቦታ የተጻፈው መረጃ ከሥር በካርድ ኮ ለሙ ውስጥ ከተፃፈው ኮድ ጋር መጣጣማቸውን ማገናዘብ ተገቢ ነው። ለዚህም በሽፋን ገጹ ላይ ያሉትን ኮዶች መመልከት ያስፈልጋል።

| ለአምድ 21 የሚያገለግል | |
|---|---|
| የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል | |
| ኮድ | የክፍል ደረጃ |
| 01. | አንደኛ ክፍል |
| 02. | ሁለተኛ ክፍል |
| 03. | ሶስተኛ ክፍል |
| 04. | አራተኛ ክፍል |
| 05. | አምስተኛ ክፍል |
| 06. | ስድተኛ ክፍል |
| 07. | ሰባተኛ ክፍል |
| 08. | ስምተኛ ክፍል |
| 09. | ዘጠነኛ በቀድሞ |
| 10. | አሥረኛ በቀድሞ |
| 11. | አስራ አንደኛ በቀድሞ |
| 12. | አስራ ሁለተኛ ቀድሞ |
| 13. | ዘጠነኛ በአዲሱ |
| 14. | አስረኛ በአዲሱ |
| 17. | 10+1/በአዲሱ የሙያ/ |
| 18. | 10+2/በአዲሱ የሙያ/ |
| 19. | 10+2 ያልጨረሱ |
| 20. | ሰርተፊኬት |
| 22. | ዲግሪ ያልጨረሱ |
| 24. | ዲግሪ የጨረሱ |
| 25. | ከዲግሪ በላይ |
| 95. | መሠረተ ትምህርት |
| 96. | መደበኛ ያልሆኑ |

## ዓምድ 22-24:- የሥልጠና ሁኔታ (ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ብቻ)

ከዚህ ዓምድ በኋላ ያሉት ተከታታይ ዓምዶች የሚመለከታቸው ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ግለሰቦች ብቻ ስለሆነ ከ10 ዓመት በታች ለሆነው የቤተሰብ አባል መረጃ ተሞልቶ አለመምጣቱንና በስህተት ተሞልቶም ከመጣ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ አሳይቶ መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል:: በአንፃሩም ከ10 ዓመት በላይ ለሆነው ግለሰብ መረጃ ተሞልቶ መምጣት ሲገባው ሳይሞላ ከመጣ ለተቆጣጣሪ ማሳየትና ተገቢው ኮድ እንዲሞላ ማድረግ ያሻል::

## ዓምድ 22:- የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ሥልጠና ወስደውና አጠናቀው የምስክር ወረቀት ወ ይም ከዛ በላይ አግኝተዋል?

በዚህ ዓምድ በሚገኘው ካርድ ኮለም አዎን ለመለሱ ኮድ 1፣ የለም ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋ ገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም በዚህ ዓምድ የለም መልሰው ኮድ 2 የተሞላላቸው የሚቀጥሉት ዓምዶች ማለ ትም ከዓምድ 23 እስከ ዓምድ 24 ሳይሞላላቸው በሰረዝ ታልፈው ወደ ዓምድ 25 መሸጋገራቸውን ማረጋገ ጥ ተገቢ ነው:: በሌላ መልኩ ደግሞ በዓምድ 21 ላይ ሠርተፊኬት፣ዲኘሎማ የጨረሱ፣ዲግሪ እንዲሁም ዲግሪና ከዚያ በላይ ተሞልቶ ከሆነ በዚህም ዓምድ የግድ ተሞልቶ መምጣት ስለሚኖርበት በዚህ ሁኔታ መሞላቱን ማየት ያሻል:: ይህ ዓምድ ሳይሞላ ከመጣ በዓምድ 21 ላይ ከተሞላው መረጃ ጋር በማገናዘብ መሙላት ይቻላል:: ይህም ሲደረግ ተቆጣጣሪው ማየት አለበት::

## ዓምድ 23:- የሰለጠኑበት የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ዓይነት ምንድ ነው?

በዓምድ 22 የሰለጠኑበት የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ሥልጠና ወስጀና አጠናቅቄ የምስክር ወረቀት ወይም ከዛ በላይ አግኝቼአለሁ ብለው መልሰው ኮድ 1 የተሞላላቸው በዚህ ዓምድ የሰለጠኑበት የሙያ (ቮኬሽናል/ ቴክኒካል) ዓይነትና ተገቢው ኮድ በካርድ ኮለሙ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የሙያ ዓይነቶቹንና ተገ ቢውን ኮድ ለማገናዘብ ከታች የቀረበውን ዝርዝር ይመልከቱ::

## ዓምድ 24 . ስራውን የሚሰሩት በሠለጠኑበት ሙያ/ መስክ ነውን ? ካልሰሩ ለምን ?

በዚህ ዓምድ የሚጠየቁት ግለሰቦች የሙያ ስልጠና ወስደውና በዓምድ 22 "አዎን" ብለው የመለሱ ሲሆን፣ በዚህ ጥያቄ ደግሞ በሰለጠኑበት ሙያ አሁን እየሰሩ እንደሆነና እንዳልሆነ ተጠይቀዋል:: ስለሆነም እየሰሩ ከሆነ ኮድ "00" ተሞልቶ "እየሰራሁ" ነው የሚል ደግሞ መፃፉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በሌላ ሁኔታ ላይ ላሉ ደግሞ ከተሰጡት አማራጭ መልሶችና ተገቢው ኮድ መሞላቱንና ይህም ከ01-11 ባለው ውስጥ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል::

## ዓምድ 25፡- የጋብቻ ሁኔታ ?

ይህ ዓምድ እንደ «ሥልጠና ሁኔታ» የሚሞላው ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤ ተሰቡ አባላት ብቻ ስለሆነ ከ10 ዓመት በታች ለሆኑ ግለሰቦች ሳይሞላ መምጣቱን፤ በስህተት ተሞ ልቶም ከመጣ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ አሳይቶ መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል:: በአንፃሩም ከ1 0 ዓመት በላይ ለሆነው ግለሰብ መረጃ ተሞልቶ መምጣት ሲገባው ሳይሞላ ከመጣ ለተቆጣጣሪው ማሳየትና ተገቢው ኮድ እንዲሞላ ማድረግ ተገቢ ነው:: በተጨማሪም በካርድ ኮለም ውስጥ ተሞ ልተው የመጡት ቁጥሮች ከኮድ 1-5 ከተዘረዘሩት ውጭ እንዳልሆነ ማየት ያስፈልጋል::

## ዓምድ 26-27- የሴቶች የወሊድ ሁኔታ /ዕድሜአቸው 15 ዓመትና በላይ ለሆናቸው

እነዚህ ዓምዶች ዕድሜያቸው 15 ዓመትና በላይ የሆናቸው ሴቶች ብቻ ስለ ወሊድ ሁኔታቸው የሚጠየቁበት ሲሆን፣ እድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች ለሆነና ለሁሉም ወንዶች ዓምዶቹ በሠረዝ እንደሚታለፍ ማወቅ ያስፈልጋል::

### ዓምድ 26፡- እስካሁን ምን ያህል ልጆች ወልደዋል?

ለዚህ ጥያቄ ዕድሜያቸው 15 ዓመትና በላይ የሆናቸው ሴቶች እስካሁን ድረስ ምን ያህል ልጆች ወልደው እንደሆነ ተጠይቀው መልሶቻቸውም በፆታ በመክፈል የተሰጡት ካርድ ኮለሞች ውስጥ ተሞልተዋል:: ከዚህም አንፃር ወይም ልጅ ሳልወለዱ ሴቶች ኮድ "00" የተሞላ ሲሆን፣ ልጆች ወልደው ለሚያውቁ ደግሞ የወለዱት ብዛት ተሞልቶ መጥቷል:: እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ነገር ተሞልቶ የመጣው መረጃ ከመልስ ሰጪዎቹ ዕድሜ ጋር በማነፃፀር የተሞላው የልጆች ብዛት ከሴትዮዋ ዕድሜ ጋር ሲተያይ አሳማኝና የሚመስል መሆኑን ማጣራት ያስፈልጋል::

### ዓምድ 27፡- ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በሕይወት የተወለደ ልጅ ተገላግለዋል?

ለዚህ ዓምድ መልስ የሚሰጡ ግለሰቦች ማለትም ባለፉት 12 ወራት በሕይወት የተወለደ ልጅ ለተገላገሉ ሰዎች የሚሞላው የተገላገሉት የልጅ ብዛት ይሆናል:: ስለዚህ እንደአጋጣሚ ሆኖ ሴቶች ከአንድ በላይ ልጆች ሊወልዱ ስለሚችሉ ከአንድ በላይ ቁጥር ተሞልቶ ቢመጣ የመረጃ ሰብሳቢው ስህተት ሆኖ እንዳይቆጠር ይህንን መገንዘብ ያሻል:: ከዚህ በተለየ ደግሞ ምንም ልጅ ሳልወለዱ ኮድ 0 ተሞልቶ መጥቷል::

በዚህ ዓምድ ላይ ልጁ ወልደው የተሞላላቸው ሰዎች ቢገኙና በዓምድ 26 ላይ ግን 00 ተሞልቶ ቢሆን ቢያንስ በዚህ ዓምድ የተሞላው የልጁ ብዛት በዓምድ 26 መሞላት ስለሚገባው ሁኔታውን ለተቆጣጣሪው በማሳወቅ መፍትሔ በጋራ መሻት ይበጃል::

# <u>ክፍል 3፡-</u> ያለፉት 7 ቀናት የሥራ ሁኔታ

<u>(ከዓምድ 28-39 ዕድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ)</u>

**<u>ዓምድ 11፡-</u> <u>መሉ ስም፡</u>-** ይህ ዓምድ ከገጽ 1 ዓምድ 11 በቀጥታ የሚወራረስ ነው:: ስለሆም በዚህ ዓምድ የተዘረዘሩት የቤተሰብ አባላት ስም ዝርዝር በገጽ 1 ዓምድ 11 ከተዘረዘሩት ጋር አንድ ዓይነት መሆናቸውን ማመሳከር ያስፈልጋል:: በተለይም የስሞች አመዘጋገብ በሁሉም ገጾች በተመሳሳይ ቅደም ተከተል መሆኑ መረጋገጥ አለበት:: ይኸም የሚያስፈልገው መረጃ አግድም Key ስለሚደረግ የአንዱ መረጃ ለሌላው እንዳይፃፍ ነው::

**<u>ዓምድ 10፡-</u> <u>የመስመር ቁጥር፡</u>-** ቀድሞ የተሞላ ስለሆነ አይነካም::

ሆኖም የቤተሰቡ አባላት ከ11 በላይ በመሆናቸው በተጨማሪነት ጥቅም ላይ የዋለ መጠይቅ መሆኑ ከተረጋገጠ እና ተራ ቁጥሮቹ በመስክ ላይ ካልተስተካከሉ አራሚው በተጨማሪ መጠይቅ ላይ « 01» ወደ «12»፣ «02» ወደ «13» በመቀየር ማረም ይኖርበታል::

**ዓምድ 28 <u>ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በምርታማ ሥራ ማለትም ተቀጥረው በክፍያ ወይም ትርፍ ለማግኘት ወይም በቤተሰብ ድርጅት ውስጥ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ ተሠማርተው ነበርን ?</u>**

ይህ ጥያቄ ከዚህ በኃላ ለሚመጡ ጥያቄዎችና ክፍሎች መነሻና መሠረታዊ ጥያቄ ስለሆነ በጥንቃቄ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ስለሆነም ከላይ ከተዘረዘሩት ምርታማ ሥራዎች ቢያንስ በአንዱ ለተሰማራ የቤተሰብ አባል የሰራው <u>የስራ ዓይነት ተፅፎ</u> አዎን» የሚለው ኮድ 1 መሞላቱን በአንፃሩም በአንዱም እንኳን ላልተሰማራ «የለም» የሚለው ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ስለዚህ በካርድ ኮለሞቹ ውስጥ መታየት የሚገባቸው ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ብቻ መሆን አለባቸው:: በተጨማሪም«የለም» መልሰው ኮድ 2 የተሞላላቸው ቀጣዩን ዓምድ 29 ሳይሞላ ወደ ዓምድ 30 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

**ዓምድ 29 : <u>የምሣና የጉዞ ሰዓትን ሳይጨምር ባለፉት 7 ቀናት በሰሩዋቸው በሁሉም ምርታማ ሥራዎች ለስንት ሰዓት</u> <u>ሰርተዋል</u> ? የትርፍ ሰዓትን ያጠቃልላል::**

ይህ ዓምድ በእያንዳንዱ ቀን የተሰራ የሥራ ሰዓት መጠን በተለየ ማስታወሻ ከተያዘ በኂላ ወደዚህ የተመዘገበበት ነው:: እንደ ዓምድ 28 ሁሉ ይህም ዓምድ መሠረታዊ ነው:: ምክንያቱም በሳምንት ውስጥ በሠሩት የሥራ ሰዓት መጠን ላይ ተመርኩዘን የቤተሰብ አባላትን ሥራ ያላቸው፣ ሥራ አጥ ወይም ከሁለቱም ውጭ ለመከፋፈል ስለሚረዳ ነው:: ስለዚህ በዚህ ዓምድ ያሉት መረጃዎች በጥንቃቄ መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: እንዲሁም ክፍልፋይ ሰዓቶች ተጠጋግተው በሙሉ ቁጥር መጻፍ አለባቸው:: «የሳምንቱ ምርታማ ስራ ሰዓት በሚለው ንዑስ አምድ ውስጥ ተሞልቶ የመጣው ቁጥርና «97» እና ከዛ በላይ ከሆነ በዚሁ ዓምድ ሥር መታየት ያለበት ቁጥር «97» ነው::

ይህ ካልሆነ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት መረጃውን ማስተካከል ያስፈልጋል:: በተቻለ መጠን በነዚህ ዓምዶች ኮድ 99 እንዳይሰፍር ይፈልጋል:: ምክንያቱም በአንድ ቦታ እንኳን ኮድ 9 ካለ ድምሩ (በታቡሌሽን) ወቅት 99 ስለሚደረግ ነው::

**ዓምድ 30:-** **ባለፉት 7 ቀናት ለራስዎ/ ቤተሠብዎ ፍጆታ የሚውልን የማገዶ እንጨት ለመሰብሰብ ምን ያህል ሠዓት አውለዋል?**

ይህ ዓምድ ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰብ አባላት ተጠይቀዋል:: እናም በዚሁ ዓምድ ላይ መሞላት የሚገባው ሰዓት ከ"00" እስከ '97' ሲሆን፣ ኮድ 98 ደግሞ እንጨት ለማይለቅሙ የቤተስብ አባላትና በእንጨት ለማይጠቀሙ የቤተሰብ አባላት ተሞልቷል:: ስለዚህም ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ የተሞላ ቁጥር /ኮድ/ ከተገኘ ስህተት ስለሆነ መስተካከል ይገባዋል::

**ዓምድ 31:-** **ባለፉት 7 ቀናት ለራስዎ/ ቤተሰብዎ ፍጆታ የሚውልን ውሃ ለመቅዳት ምን ያህል ሠዓት አውለዋል?**

ይህ ጥያቄም እንደ ዓምድ 30 ሁሉ የተሞላው የሰዓት መጠን ከ00-97 ሲሆን፣ ኮድ 98 ደግሞ ውሃ ለማይቀዱ የቤተሰብ አባላት እና በግቢ/በቤት ውስጥ ወሃ ላላቸው ቤተሰቦች የተሰጠ ኮድ ስለሆነ ከነዚህ የተለየ ኮድ ያለመሞላቱን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል::

**ዓምድ 32:-** **ባለፉት 7 ቀናት የቤት ውስጥ ሥራ በሳምንት ለስንት ሰዓት ሰርተዋል?**

በዚህ ጥያቄ ሁሉም ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰብ አባላት ፆታ ሳይለይ የተጠየቁ ሲሆን፣ በዓምድ 30 እና 31 እንደተሞላው የሰዓት መጠን ከ00 እስከ 97 መሞላት የሚችል ሲሆን፣ ምንም ላልሰሩም/ለማይሰሩም ቢሆን ኮድ /የሰዓቱ /መጠን 00 እንጂ 98 አለመሞላቱ መታየት ይኖርበታል::

**ዓምድ 33:-** **ባለፉት 7 ቀናት በምርታማ ስራ የሰሩት የስራ ሰዓት ድምር ስንት ነው?**

ለዚህ ጥያቄ በመጠይቁ ላይ የቀረቡት አማራጮች 2 ሲሆኑ እነዚህም ኮድ2 4 ሰዓትና በላይ፤ ኮድ 1. ከ4 ሰዓት በታች ወይም አልተጠየቁም የሚሉ ናቸው:: ስለዚህ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ካርድ ኮለም ተሞልቶ የመጣው ቁጥር ኮድ «1» ወይም ኮድ «2» ብቻ መሆን አለበት::
ከዚያም ከ4 ሰዓት በላይ ሰርተው ኮድ «2» የተሞላላቸው የሚከተሉትን ሁለት አምዶች ማለትም አምድ 34 እና አምድ35ን ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 36 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

**ዓምድ 34:-** **ሥራ እያለዎት ነበር ባለፉት 7 ቀናት በሥራ ላይ ያልተሰማሩት?**

በመጀመሪያ ይህ ዓምድ ላይ መረጃ ተሞልቶ የሚመጣው በዓምድ 28 ኮድ 2 ለተሞላላቸው እና በዓምድ 28 ኮድ 1 የተሞላላቸው ቢሆንም፣በአጠቃላይ በሳምንት ውስጥ የሠሩት
የሥራ ሰዓት መጠን ከ4 ሰዓት በታች ለሆነ በዓምድ 29 ኮድ «1» ለተሞላላቸው የቤተሰብ አባላት ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል :: ስለዚህ ከ4 ሰዓት በታች ለሠሩ እና ምንም ስራ ላልሠሩ የቤተሰብ አባላት ሥራእያላቸው ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በሥራ ላይ ካልተሠማሩ አዎን የሚለው ከኮድ «1-3» ሲሞላ ነገር ግን ሥራ ሳይኖራቸው ከሆነ የለም የሚለው ኮድ «4» ሊሞላላቸው ይገባል:: በመጨረሻም በዚህ ዓምድ የለም ብለው ኮድ «4» የተሞላላቸው ግለሰቦች እሰከ ዓምድ 56 ድረስ ምንም መረጃ ሳይሞላላቸው በቀጥታ ወደ ዓምድ 56 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

**ዓምድ 35:- ባለፉት 7 ቀናት ሥራዎን ያልሰሩበት ዋና ምክንያት ምንድነው?**

በዚህ ዓምድ መረጃ ተሞልቶ ሊመጣላቸው የሚገባ የቤተሰብ አባላት በዓምድ 34 ኮድ «1-3»የ ተሞላላቸው ማለትም ሥራ እያላቸው በሥራ ላይ ያልተሠማሩ ናቸው:: ባለፉት 7 ቀናት ውስ ጥ ከሥራ ሊያስቀሯቸው ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ 6 አማራጭ መልሶች በዚህ ዓምድውስጥ ተዘርዝረዋል:: ስለሆነም ምክንያትና በዓምድ የተሰጠው ከሥሩ በሚገኘው ካርድ ኮለም የተሞላ ው ኮድ ትክክል መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል:: ከተዘረዘሩት የተለየ መልስ ተሰጥቶ ከሆነ ኮድ 7 ተሞልቶ መገለፁን ማየት ያሻል:: የካርድ ኮለመ ውስጥ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከ1-7 ውጭ መሆን የለባቸውም:: በመጨረሻም በዚህ ዓምድ መረጃ የተሞላላቸው ግለሰቦች ሁሉም ቀጣዩን ዓምድ 36 መጠየቃቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

**ዓምድ 36 - 39 :- <u>የሥራ ዓይነት፣ የድርጅት ዋና ምርት/ አገልግሎት፣ የቅጥር ሁኔታ/Employment Status/ እና የሥራ ቦታ</u>**

እነዚህ ዓምዶች የሚሞሉት በጥናቱ ሳምንት በአጠቃላይ የሠሩት የሥራ ሰዓት መጠን ቢያንስ 4 ሰ ዓት ለሆነ ማለትም በዓምድ 29 ኮድ «2» ለተሞላላቸው ግለሰቦች፣ባለፉት 7 ቀናት ስራ እያላቸው ላልሰሩ እና ምንም እንኳን በጥናቱ ሳምንት በአጠቃላይ የሠሩት ሥራ ሰዓት መጠን ከ4 ሰዓት በታች ቢሆንም ሥራ እያላቸው ላልሠሩ ግለሰቦች ጭምር ነው:: ስለዚህ በዓምድ 29 ኮድ 2 ወይም በዓምድ 33 ላይ ከኮድ1-3 የተሞላላቸው በዚህ ክፍል ከዓምድ35-55 ድረስ መረጃዎች ተሞልተውላቸው መምጣታቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

**ዓምድ 36:** **<u>ባለፉት 7 ቀናት የሰሩት የዋነኛ ስራዎ ዓይነት ምንድነው ?</u>**

በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ለነበሩና ሥራ ኖሯቸወ ነገር ግን በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ያልነበሩ ግለሰቦች (በዓምድ 34 ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው) በዚህ ዓምድ የዋነኛ ሥራቸው ዓይነት ተሞልቶ መጥቷል:: ለዚህ ዋነኛ የሥራ ዓይነት ተገቢ የሆነው የመለያ ኮድ "የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ምደባና ኮድ ዝርዝር" ተብሎ ከተዘጋጀው መጽሐፍ በመውሰድ ኮዱ የተሞላ ቢሆንም የኤዲተሮች ዋና ሥራ የሚሆነው የኮዱን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ነው:: የዋነኛ የሥራ ዓይነት ከኮድ ዘርዝር መጽሐፍ ውስጥ መጣጣም ካልቻለ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት ቢቻል ተቀራራቢ የሆነውን የሥራ ዓይነት ኮድ መሙላት ያስፈልጋል:: አንዳንድ ጊዜ በመስክ የተሞላው የሥራ ዓይነት ግልፅና በቀላሉ የማይነበብ ለመረዳትም አስቸጋሪ ከሆነ ኢዲተሩ በእርጋታና በትዕግስት መረጃ ሰብሳቢው የሞላውን ማጣራት ይኖርበታል:: ከዚህም በተጨማሪ ከሥራ ዓይነት ኮድ ዝርዝሩ ጋር ለማገናኘት ሲሞክር በቅድሚያ የተጠቀሰው የሥራ ዓይነት በየትኛው ዋና ክፍል እንደሆነ መለየት ከዚያም በዋና ክፍሉ ሥር ከተዘረዘሩት የሥራ ዓይነቶች ለየትኛው እንደሚቀርብ አመዛዝኖ ኮድ ማድረግ ያስፈልጋል:: በሆኑም ለመወሰን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በመጠራጠር ኮድ ከማድረግ መቆጠብና ተቆጣጣሪውን በማማከር ትክክለኛ ውን ኮድ መስጠት ይገባል:: ስለዚህ በኮድ ዝርዝሩ ከተሰጠው የማይጣጣም ሆኖ ከተገኘ ከተቆጣጣሪውና ከአሰሪው ክፍል ጋር ተነጋግሮ አዲስ ኮድ መስጠት ሊያስፈልግ ይችላል::

**ዓምድ 37:-** <u>ይህንን ሥራ የሚሰሩት የት ነው ?</u>

በዚህ ጥያቄ አያሌ ሰዎች ሊሠሩበት ይችላሉ የተባሉት ዋና ዋና የሥራ ቦታዎች ከኮድ 0 እስከ 8 ድረስ የተሞላ ሲሆን፣ ከነዚህ ኮዶች ውጭ ከተሞላ ግን ስህተት ስለሆነ መስተካከል ይኖርበታል:: በተመሳሳይ መልኩም ሌላ ተብሎ ኮድ 8 የተሰጠው ካለ ከ0-እስከ 7 ካለው ውስጥ የሚካተት ከሆነ በዚሁ ኮድ እንዲካተት ማድረግ ያሻል::

**ዓምድ 38** <u>በዋነኛነት የሚሰሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት ምንድነው?</u>

በተመሳሳይ ሁኔታ በጥናቱ ሳምንት በሥራ ላይ ለነበሩና ሥራ ኖሯቸው በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ላልነበሩ ግለሰቦች በዚህ ዓምድ በዋነኝነት የሚሰሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት /ኢንዱስትሪ/ ተሞልቶ መጥቷል:: ለዚህ የኢንዱስትሪ ዓይነት ተገቢ የሆነው የመለያ ኮድ ከ"<u>የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት</u> <u>ኮድ ዝርዝር</u>" ተብሎ የተዘጋጀው መጽሐፍ በመውሰድ ኮድ ተሞልቷል::ኤዲተሩ ይህ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል:: የኢንዱስትሪ ነገር ግን በመስክ ላይ የተሞላው የድርጅት ምርት/አገልግሎት ሳይሆን የድርጅቱ ስም ወይም ሌላ መግለጫ ሊሆን ይችላል:: በዚህን ጊዜ ከተቆጣጣሪው ጋር በመመካከር የድርጅቱ ዋና ምርት/አገልግሎት ምን እንደሆነ ለማወቅ የተለያዩ ግንዛቤዎችንና ሁኔታዎችን በመውሰድ ለመሙላት ይሞከራል::

**ዓምድ 39** <u>**የዋነኛ ሥራዎ የቅጥር (Employment Status) ሁኔታ ምንድነው ?**</u>

ለዓምዱ የተሰጠው ክፍት ቦታ ተሞልቶ የመጣው የቅጥር ሁኔታ ከሥር በካርድ ኮለሙ ከተሞላው ኮድ ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም ከጥያቄው ሥር የተዘረዘሩት 12 አማራጭ መልሶች ከኮድ 01-12 ብቻ ስለሆኑ ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ ሳይሞላ መምጣቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: እንዲሁም ከኮድ 08-12 የተሞላላቸው ግለሰቦች ተከታዮቹን ዓምዶች ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 46 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ሲገባ ኮድ 07 የተሞላላቸው ደግሞ ወደ ዓምድ 47 መሸጋገራቸውን ማጣራት ተገቢ ይሆናል:: የአማራጭ መልሶች ዝርዝር መጠይቁ ላይ ከጥያቄው ሥር ቀርበዋል::

## ከዓምድ 40-56 ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ

**ዓምድ 40:-** <u>የዋነኛ ሥራዎ የቅጥር ዓይነት ምንድነው</u>

ለዚህ ዓምድ አራት አማራጭ ኮዶች (ከጥያቄው ሥር) ቀርበዋል:: ስለሆነም ከላይ የቅጥር ዓይነቱ፣ ከሥር በሚገኘው ካርድ ኮለም ደግሞ ተስማሚው ኮድ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም በካርድ ኮለሙ ውስጥ ተሞልተው የመጡት ኮዶች ከ1-5 ውጭ መሆን የለባቸውም::

ዓምድ 41-45:- /ከቅጥር ስራ የተገኘ ክፍያ/ በዓምድ 39 ከኮድ 01 - 06

ዓምድ 41:- ለሥራዎ የሚከፈልዎት በገንዘብ ነው ወይስ በዓይነት?

በዚህ ዓምድ ጥያቄው የተጠየቀላቸው ከላይ በዓምድ 39 ከኮድ 01-06 ለተሞላላቸው ስለሆነ ከነዚህ ኮዶች ውጭ (07-12) የተሞላላቸው ግን ይህንን ዓምድ አለመጠየቃቸውንና ከተጠየቁም በጥንቃቄ ታርሞ ተገቢው ኮድ እንዲሞላላቸው ማድረግ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም ለዚህ ጥያቄ ለተሰጡት 3 አማራጭ መልሶች የተዘጋጁት 3 ኮዶች በመሆናቸው ከነዚህ ውጭ በተከታታይነት ተሞልተው ከመጡት ሌሎች መረጃዎች ጋር በማገናዘብ ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን ማስተካከል ተገቢ ይሆናል:: አማራጭ መልሶቹ ከጥያቄው ስር ስለተዘረዘሩ የተሞላውን ኮድ ተመሳሳይነትም ማገናዘብ ይገባል::

ዓምድ 42:- ለዋናው ሥራዎ የአከፋፈል ጊዜ እንዴት ነው ?

ይህ ጥያቄ ግለሰቦች በዓምድ 39 ከኮድ 01-06 ተሞልቶላቸው ከሆነ ብቻ ነው የሚጠየቁት ስለሆነም እነዚህ ግለሰቦች ብቻ መጠየቃቸው መረጋገጥ ይኖርበታል:: ለዚህ ጥያቄ ለተሰጡት ሰባት አማራጭ መልሶች ከ1-7 ኮድ ተሰጥቶአቸው ከጥያቄው ስር ተዘርዝረዋል:: ስለሆነም፣ በዓምዱ ስር በጽሁፍ የተገለፀው የአከፋፈል ጊዜና በካርድ ኮለሙ የተሞላው ኮድ መጣጣማቸው ይረጋገጣል:: በመጨረሻም ከኮድ 5-7 የተሞላላቸው ቀጣዮቹን /ሁለት ጥያቄዎች ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 45 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል::

ዓምድ 43:- በገለፁልኝ የአከፋፈል መሠረት ባለፈው ወር ለስንት የአከፋፈል ጊዜያት ሠርተዋል?

በዚህ ጥያቄ ግለሰቦች በዓምድ 39 ከኮድ 01-06 የተሞላላቸው ብቻ መጠየቃቸው ይረጋገጣል:: ጥያቄው በዓምድ 42 በተገለፀው የአከፋፈል ጊዜ መሠረት ለምን ያህል ጊዜ እየተከፈላቸው መሥራታቸውን ተጠይቀው ተሞልቷል በዚህ መሠረት በዓምዱ ሦስት ካርድ ኮለም ተሰጥቷል:: ስለሆነም በዓምድ 42 በየቀኑ ብለው ኮድ "2" የመለሱ በዚህ ዓምድ (በዓምድ 43) ላይ ከ30፣ በየሳምንቱ ኮድ "3" ለተሞላለት ደግሞ ከ4 እንዲሁም በየ15 ቀኑ ብሎ ኮድ "4" ለተሞላላት ከ2 አለመብለጡን በአትኩሮት ማየት ያስፈልጋል::

ዓምድ 44:- በዓምድ 42 በገለፁልኝ አከፋፈል መሠረት ለመጨረሻ ጊዜ ምን ያህል ተከፈልዎት?

ይህ ጥያቄ ግለሰቦች በዓምድ 42 ለገለፁት የአከፋፈል ሁኔታ በመጨረሻው ክፍያቸው ያገኙት የብር መጠን ተሞልቶ መጥቷል:: ለዚህም አራት ካርድ ኮለሞች የተዘጋጁ ስለሆነ በዚሁ መፃፊያ በተዘጋጁት ካርድ ኮለሞች ቁጥሮች ከቀኝ ወደ ግራ መሞላቱን ማረጋገጥ ወሳኝ ነው:: ይህም ማለት የብሩ መጠን በካርድ ኮለሙ ሲፃፍ መጀመር የሚኖርበት ከቀኝ ይሆናል:: ስለዚህ "30 ብር" ያለ መልስ ሰጪ ብሩ በዓምዱ ሲሰፍር "0" "0" "3" "0" መሆን ይኖርበታል:: እዚህ ላይ ከብር "9997" እና በላይ ለሚከፈላቸው "9997" ብቻ መሞላት ይኖርበታል::

**ዓምድ 45:- በዋነኛነት ለሰሩት ሥራ ባለፈው አንድ ወር ውስጥ በጠቅላላው ምን ያህል ተከፈለዎት ?**

ይህ ጥያቄ የመልስ ሰጪዎቹ ከቅጥር ሥራ የተገኘ የወር ክፍያ መጠን የተጠየቀበት ሲሆን በዓምድ 44 ከተሞላው ጋር ሊነፃፀር ይችላል፡፡ ይኸውም የአከፋፈል ጊዜው በሣምንት/አስራ አምስት ቀን የሆነ ሠራተኛ/ቅጥረኛ በዓምድ 44 ያስመዘገበው የገንዘብ መጠን ከዓምድ 45 ማነስ ወይም እኩል መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን በተመሳሳይ መልኩም በካርድ ኮለሙ ውስጥ የቁጥሮቹ አፃፃፍ ከላይ በተገለፀው መሠረት ከቀኝ በመጀመር ይሆናል፡፡ የወር ገቢያቸው ከብር "9997" እና በላይ ለሆነ የሚፃፈው ይኸው "9997" ይሆናል፡፡

**ዓምድ 46:- ድርጅቱ/የሥራ መስኩ/**

በገጠር መጠይቆች ላይ በግል የግብርና ሥራ ላይ ለተሠማሩ ግለሰቦች እና በገጠርም ሆነ በከተማ በቤት ሠራተኝነት ተቀጥረው ለሚያገለግሉ ተሞልተው የመጡት መረጃዎች በሙሉ ኮድ ማለትም ፟ አዎን የሚል መልስ እንደተሞላላቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ዓምዶች ተ ሞልተው መምጣት የሚገባቸው ለሁሉም ግለሰቦች ሳይሆን በዓምድ 39 የቅጥር ሁኔታዎች ኮድ 03 ፣ 06፣ 08፣09፣10፣11 ወይም 12 ለሆኑ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ከነዚህ ግለሰቦች ውጭ ለሌሎችም መረጃ ተሞለቶ ከመጣ ስህተት ስለሆነ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት መረጃውን መሰረዝ ያስ ፈልጋል፡፡

**A. አሥር ወይም በላይ የሥራው ተከፋይ ሠራተኞች አሉት?**

በዚህ ዓምድ ለቀረበው ጥያቄ 3 አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋል፡፡ ስለሆነም በካርድ ኮለሙ ተሞል ተው የመጡት ኮዶች ኮድ «1» ማለት «10ና በላይ» ወይም ኮድ «2» ማለትም ከ10 በታች የሚ ሉት ወይም ኮድ 3 ማለትም አላውቅም መሆን አለባቸው፡ በተጨማሪም ከላይ ለተጻፉት ቃላት ከሥር በካርድ ኮለሙ የተሞሉት ኮዶች ተገቢ መሆናቸውን ማገናዘብ ያሻል፡፡

**B. የተሟላ የሒሳብ መዝገብ አለው?**

በዚህ ዓምድ ለቀረበው ጥያቄ 3 አማራጭ መልሶች ቀርበዋል፡፡ ስለዚህ በካርድ ኮለም ተሞልተው የ መጡት ቁጥሮች ከኮድ 1፣ 2 ወይም 3 ውጭ አለሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

**C. ፈቃድ አለው ?**

ለጥያቄውም የቀረቡት አማራጭ መልሶች 3 ብቻ ስለሆኑ ከነዚህ ኮዶች ማለትም ኮድ 1፣ 2 ወይም 3 ውጭ በካርድ ኮለሙ አለመሞላቱንማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡

ዓምድ 47፡- <u>ይህ ድርጅት ወይም መሥሪያ ቤት የመጀመሪያዎ ነው?</u>

ይህ ጥያቄ ወደዚህ ክፍል የመጡ ግለሰቦችን ሁሉ ስለሚመለከት ለሁሉም ግለሰቦች መረጃ ተሞልቶ መምጣቱን ማየት ያስፈልጋል፡፡ አሁን የሚሠሩበት ድርጅት የመጀመሪያቸው ለሆኑ ግለሰቦች አዎን በማለታቸው ኮድ «1» መሞላቱኗ ከዚህ በፊት ሌላ ድርጅት ይሠሩ ለነበሩ ደግሞ የለም በማለታቸው ኮድ «2» ተሞልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ኮድ «1» «ይህ ድርጅት የመጀመሪያዬ ነው ላሉ» ተከታዩ ዓምድ ስለማይመለከታቸው ወደ ዓምድ 49 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ያሻል፡፡

ዓምድ 48 <u>ካለፈው ድርጅት/ መሥሪያ ቤት ወይም የሥራ መስክ ለምን ቀየሩ?</u>

በዚህ ዓምድ መረጃ ተሞልቶ ሊመጣ የሚገባው በዓምድ 47 የለም መልሰው ኮድ «2» ለተሞላላቸው ማለትም ይህ ድርጅት የመጀመሪያዬ አይደለም ላሉ ግለሰቦ ብቻ ነው፡፡ በዓምድ 47 ኮድ «1 » ለተሞላላቸው በዚህ ዓምድ ላይ መረጃ ተሞልቶላቸው ከመጣ መረጃው ስህተት ስለሆነ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት መረጃውን መሰረዝ ተገቢ ነው፡፡ ለጥያቄው የቀረቡት አማራጭ መልሶች 12 ብቻ ስለሆኑ በካርድ ኮለም ውስጥ ሊታዩ የሚገባቸው ቁጥሮች ከ00-11 ውጭ መሆን የለባቸውም፡፡ በዚህ ዓምድ ኮድ 11 ተሞልቶ በዓምዱ ክፍት ቦታ ምክንያት ከተመዘገበ ይህን ምክንያት በትኩረት በመመርመር ከጥያቄው ሥር ከኮድ 00-10 ከተዘረዘሩት መልሶች ጋር የሚመሳሰል ከሆነ ኮድ 11ን በመሰረዝ ተቀራራቢውን ኮድ በካርድ ኮለሙ መሙላት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ከላይ በጽሁፍ ለተገለጹት ምክንያቶች ከሥር በካርድ ካለሙ የተሞሉት ኮዶች ተገቢ መሆናቸውን ማገናዘብ ያሻል፡፡

ዓምድ 49፡- <u>አሁን በሚሠሩት ሥራ ይረካሉ? ካልረኩ ለምን?</u>

ለዚህ ጥያቄ 12 አማራጮች የተሰጡ ሲሆን ፣ መልስ ሰጪዎች እየሰሩ ባሉት ስራ መርካትና አለመርካታቸው ተጠይቀዋል፡፡ የረኩ ከሆነ ኮድ 00 የተሞላ ሲሆን፣ ካልረኩ ደግሞ ከኮድ 01- እስከ 12 ተሞልቷል፡፡ ከነዚህ ኮዶች ውጭ ከሆነ ግን ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ 50፡- <u>ባለፉት 7 ቀናት ከዋንኛው ስራዎ በተጨማሪ በሌላ ምርታማ ሥራ ላይ ተሠማርተው ነበር ?</u>

መልስ ሰጪዎች ለዚህ ጥያቄ አዎን ኮድ 1 ወይም የለም ኮድ 2 የተሞላላቸው ሲሆን፣ ከነዚህ ኮዶች ውጭ ከተሞላ ስህተት መስተካከል ይገባዋል፡፡ ተጠያቂዎች በዓምድ 28 ላይ ከአንድ በላይ ስራ ሠርተው ከነበረና እነዚሁ የሥራ ዓይነቶች በዚሁ ዓምድ ላይ ተመዝግበው ከሆነ በዚህ ዓምድ /ዓምድ 50/ ኮድ 1 መሞላት ይኖርበታል፡፡ ይኸ ሆኖ ካልተገኘ ግን ከተቆጣጣሪው ጋር በመመካከር ተዛማጅነታቸውን በማየት ማስተካከል ያሻል፡፡

ዓምድ 51፡- <u>የተጨማሪ ስራዎ/ችዎ ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት ምንድነው?</u>

የዚህ ጥያቄ አማራጮች /16/ ሲሆኑ ከነዚህ ኮዶች ውጭ አለመሞላቱ መታየት ይኖርበታል፡፡ ለዚህ ዓምድ የተሰጠው ሀሳብ ለዓምድ 38 ከተሰጠው ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም የዚህኛው ግን ባለሁለት ዲጂት /Digit/ ኮድ ሲሆን፣ የራሱ የሆነ ዓላማ ያለውም ነው፡፡

**ዓምድ 52:-** ***ባለፉት 7 ቀናት በተጨማሪ ሥራዎ/ችዋ ስንት ሰዓት ሠሩ?***

*ግለሰቦች ባለፉት 7 ቀናት በተለያዩ የምርታማ ስራ ዘርፎች ተሠማርተው እንደነበር የተጠየቁ ሲሆን፣ በዓምድ 29 ደግሞ በነዚህ ስራዎች ያጠፉትን የሰዓት መጠን ተመዝግቦላቸዋል:: በዚህ ዓምድ ደግሞ እነዚህ ሰዎች ዋነኛ ስራቸው ሆኖ ለነበረው የስራ ዓይነት የጠፋውን የሥራ ሰዓት በመቀነስ በሌሎቹ ተጨማሪ ስራዎቻቸው ምን ያህል እንደጠፋ ተጠይቋል:: ስለሆነም በዚህ ዓምድ የተሞላው የሰዓት መጠን በዓምድ 29 ከተሞላ ማነስ ይኖርበታል::*

**ዓምድ 53:-** ***ሥራ ላይ ለነበሩ***

***ባለፈው ሳምንት ተጨማሪ ሰዓት ለመሥራት ዝግጁነትና ፍላጎት ነበረዎት? /ከ4 ሰዓት በላይ ለሰሩ- በዓምድ 33 ኮድ 2 ለተሞላላቸው/***

***ሥራ ላይ ላልነበሩ***

***ባለፈው ሳምንት ለመስራት ዝግጁነትና ፍላጎት ነበረዎት? /ሥራ እያላቸው ላልሰሩ-/ በዓምድ 34 ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው/***

*ይህ ጥያቄ በዓምድ 33 ኮድ 2 ለተሞላላቸው እና በዓምድ 34 ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው ሁሉ ይጠየቅላቸዋል::በተጨማሪም ለጥያቄው የተሰጡት አማራጭ መልሶች አዎን ኮድ 1 እና የለም፣ ኮድ 2 ስለሆኑ ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ ሌላ አለመሞላቱን መታየት አለበት:: በተመሳሳይ መልኩም ኮድ 1 የተሞላላቸው ቀጣዩን ጥያቄ ሲጠየቁ ኮድ 2 የተሞላላቸው ከሆነ ወደ ክፍል 5 ይሽጋገራሉ:: ይህንንም ማረጋገጥ ያስፈልጋል::*

**ዓምድ 54** ***ተጨማሪውን ሰዓት በምን ዓይነት ሥራ መሰማራት ይፈልጉ ነበር?***

*በዚህ ዓምድ መረጃ ተሞልቶ ሊመጣላቸው የሚገባ ግለሰቦች ዓምድ 53 አዎን ብለው ኮድ «1» የ ተሞላላቸው ብቻ ናቸው: ስለሆነም በዓምድ 53 ኮድ «2» የተሞላላቸው በዚህ ዓምድ ላይ መረጃ ተሞልቶላቸው ከመጣ ስህተት ሊሆን፣ ስለሚችል ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል: የቀረቡት (ከጥያቄው ሥር) አማራጭ መልሶችም 3 ብቻ ስለሆኑ በካርድ ኮለ ሙ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከ1-3 ውጭ መሆን እንደሌለበትና በተጨማሪም በዓምዱ ክፍት ቦታ ለተጻፉት ቃላት ከሥር የተሞሉት ኮዶች ተገቢ መሆናቸውን ማገናዘብ ይገባል::*

**ዓምድ 55** ***ለምን ያህል ተጨማሪ ሰዓት መስራት ይፈልጉ ነበር?***

*ሰዎች ባለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ለምን ያህል ሰዓት ተጨማሪ ስራ መስራት ፈልገው እንደነበር ተጠይቀው ተሞልቶላቸዋል:: እናም በዚህ ዓምድ የተሞላው የሰዓት መጠን በዓምድ 29 ከተሞላው /ባለፉት ሰባት ቀናት የጠፋው የሰዓት መጠን/ ጋር ሲተያይ ልዩነቱ ምክንያታዊ መሆን ይኖርበታል:: ስለሆነም፣ በዚህ ዓምድ የተሞላው የሰዓት ብዛት ከዓምድ 29 ጋር ሲደመር የተጋነነ መሆን የለበትም:: በተመሳሳይ መልኩም በዚህ ዓምድ ከ97 በላይ ቁጥር መታየት አይኖርበትም:: የተሞላውም መጃ የአንድ ሳምንት ድምር እንጂ የአንድ ቀን አለመሆኑንም ማረጋገጥ ያሻል::*

በሌላ መልኩ ደግሞ ከ4 ሰዓት በታች ሰዓት ከተሞላ ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን ሌላ ማስታወሻ ተፅፎ ከሆነ በማየት ለማረም ይሞከራል፡፡ ይኸም የሚሆነው በአንድ ቀን ብቻ የሰዓቱ መጠን ተመዝግቦ ሊሆን ስለሚችል ነው፡፡ በመጨረሻም በዚህ ዓምድ መረጃ የተሞላላቸው ሁሉም ግለሰቦች ዩን ክፍል ዘለው በቀጥታ ወደ ዓምድ 67 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

# ክፍል 4፡- ሥራ አጥነትና የሥራ አጦች ባህሪይ

**ዓምድ 10፡- ሙሉ ስም፡-** እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ሙሉ ስም ከገጽ 1 ዓምድ 11 በትክክል መወራረሱን ማገናዘብ ይገባል፡፡

**ዓምድ 11፡- የመሥመር ቁጥር፡-** ቀድሞ የተሞላ ስለሆነ ምንም አይነካም፡፡

## ዓምድ 56 – 66A፡- ሥራ አጥነት

## ዓምድ 56፡- ባለፉት 3 ወራት ሥራ ለማግኘት ወይም የግል ሥራ ለመጀመር ጥረት አድርገው ነበር?

መጀመሪያ በዚህ ዓምድ ላይ መረጃ የሚሞላላቸው በክፍል 3 ዓምድ 34 ላይ የለም መልሰው ኮድ «4» ለተሞላላቸው ግለሰቦች መሆኑን ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ለሌሎች ግለሰቦች ግን ካርድ ኮለሞቹ በሠረዝ «-» ይታለፋሉ፡፡

ለዚህ ዓምድ የቀረቡት አማራጮች አዎን ብለው ለመለሱ ኮድ «1» እና የለም ላሉ ኮድ «2» ስለሆኑ በተገቢው ካርድ ኮለም ከሁለቱ ኮዶች አንደኛው ብቻ መሞላቱን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ከዚያም የለም ብለው ኮድ «2» የተሞላላቸው ዓምድ 57ን ተሻግረው ወደ ዓምድ 58 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

**ዓምድ 57፡- ሥራ ለማግኘት ወይም ለመጀመር ምን ጥረት አደረጉ?**

ይህ ዓምድ የሚሞላው በዓምድ 56 ኮድ «1» ለተሞላላቸው ማለትም ሥራ ለማግኘት ጥረት አድርጌ ነበር ላሉ ግለሰቦች ብቻ ነው፡፡ ከዓምዱ ግርጌም 8 አማራጭ መልስ ሊሆኑ የሚችሉ ኮዶች ቀርበዋል፡፡ ስለዚህ ከላይ ባለው ክፍት ቦታ ግለሰቡ ያደረጉት ጥረት ከሥር ባለው ካርድ ኮለም ደግሞ ተገቢው ኮድ ተሞልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ ከዚያም በዚህ ዓምድ ላይ መረጃ የተሞላላቸው ግለሰቦች ሁሉም ወደ ዓምድ 59 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያሻል፡፡

**ዓምድ 58:- ለምንድነው ሥራ ለመሥራት ወይም ለማግኘት ጥረት ያላደረጉት ?**

በመጀመሪያ ይህ ዓምድ የሚሞላላቸው በዓምድ 56 ኮድ 2 ለተሞላላቸው ማለትም ሥራ ለማግኘት ምንም ጥረት ላላደረጉ ግለሰቦች ብቻ ነው፡፡ ሥራ ለመሥራት ወይም ለማግኘት ጥረት ያላደረጉበ

ት ምክንያት በዓምዱ ግርጌ ከተዘረዘሩት 12 አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱ በዓምዱ ሥር መሞላቱንና ተገቢው ኮድ ደግሞ በካርድ ኮለሞቹ መሞላቱን ማረጋገጥ ያሻል:: የተሰጡት ኮዶች ከ01 – 12 ስለሆኑ በካርድ ኮለሞቹ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከነዚህ ውጭ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

**ዓምድ 59:-** <u>በሚቀጥለው 1 ወር ውስጥ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ቢያገኙ ይሰራሉ?</u>

ለዚህ ጥያቄ አዎን ብለው የመለሱ ግለሰቦች ኮድ «1» የለም ብለው ለመለሱ ደግሞ ኮድ «2» እንደተሞላላቸው በተጨማሪም በካርድ ኮለም ውስጥ መታየት የሚገባቸው ቁጥሮችም ከነዚህ ውጭ እንዳልሆኑ ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ከዚያም የለም ብለው መልሰው ኮድ «2» የተሞላላቸው ተከታዩን ዓምድ 60ን ዘለው ወደ ዓምድ 61 መሻገራቸውን ማየት ያስፈልጋል::

**ዓምድ 60:-** <u>በአቅምዎ ተቀጥረው ሊሰሩት የሚችሉት ስራ ቢገኝልዎት ወይም በግል ሥራ ለመሰማራት አስፈላጊ ነገሮች ቢሟሉ ስራ ለመጀመር ዝግጁ ነዎት? ከሆነ የት?</u>

በዚህ ዓምድ ለቀረበው ጥያቄ 6 አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉ መልሶች ከኮድ 1 – 6 የተሰጡ ስለሆነ በካርድ ኮለሙ ተሞልቶ የመጣው ኮድም ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ አለመሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: ከዚያም ኮድ 2፣ 3፣ 4፣ 5 ወይም ኮድ 6 የተሞላላቸው ግለሰቦች ተከታዮቹን ሁለት ዓምዶች ዘለው ወደ ዓምድ 63 መሻገራቸውን ማየት ይገባል፡

**ዓምድ 61:-** <u>ለምንድነው ሥራ ቢያገኙ የማይሰሩት?</u>

በዓምድ 60 ላይ ሥራ ቢገኝላቸው ለመሥራት ዝግጁ አይደለሁም ብለው ኮድ 1 የተሞላላቸው ግለሰቦች በሙሉ በዚህ ዓምድ ለምን ሥራ ቢያገኙ እንደማይሠሩ በዓምዱ ሥር ከተዘረዘሩት አማራጮች አንዱና ዋነኛው ምክንያት ይሞላል:: ከተዘረዘሩት 8 አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱ በዓምዱ ሥር ተጽፎ ተገቢው ኮድ ደግሞ ከሥር ባለው ካርድ ኮለም ላይ መሞላት አለበት:: ስለዚህ ካርድ ኮለሙ ውስጥ ተሞልቶ የመጣው ቁጥር ከ1–8 ካሉት ውጭ አለመሆኑና ኮዱም ለምክንደ ተገቢው መሆኑን ማረጋገጥ ያሻል:: ከዚያም ከኮድ 2–8 የተሞላላቸው በሙሉ ወደ ዓምድ 67 መተላለፋቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

**ዓምድ 62** <u>ለምን ከቤት ውስጥ ሥራ ውጭ መስራት አይፈልጉም?</u> (በዓምድ 61 ኮድ 1 ለተሞላላቸው( በቤት ውስጥ ስራ ለተሰማሩ))

በዓምድ 61 ላይ ሥራ ባገኝ የማልሠራው ያለክፍያ የቤት ውስጥ ሥራ ላይ ስለተሠማራሁ ነው ላሉ ማለትም ኮድ 1 ለተሞላላቸው በዚህ ዓምድ ለምን ከቤት ውስጥ ሥራ ውጭ መሥራት እንዳልፈለጉ ተጠይቆ ከጥያቄው ሥር ከተዘረዘሩት አማራጭ ኮዶች ውስጥ አንዱና ዋንኛው ተሞልቶ መጥቷል:: ስለዚህ ከላይ ባለው ክፍት ቦታ ላይ ለተሞላው ምክንያት ተገቢው ኮድ መሞላቱንና ከሥር ተሞልቶ የመጣው ኮድም ከ1–7 ከተዘረዘሩት ኮዶች ውጭ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በመጨረሻም ይህንን ዓምድ የተጠየቁ ግለሰቦች በሙሉ በዚህ ክፍል ያሉ ተከታይ ጥያቄዎች ስለማይመለከቷቸው ሁሉም ወደ ዓምድ 67 መተላለፋቸውን በጥንቃቄ ማየት ያስፈልጋል::

## ዓምድ 63፡- <u>የሚፈልጉት ሥራ ምን ዓይነት ነው?</u>

በመጀመሪያ ይህ ዓምድ ተሞልቶ የመጣው በዓምድ 60 ላይ ከኮድ 2-6 የተሞላላቸው ግለሰቦች ብቻ መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡ በዓምዱም ተሞልቶ የመጣው መረጃ ከጥያቄው ሥር ከተዘረዘሩት 5 አማራጭ መልሶች ውጭ አለመሆኑንና ለመልሱም ተገቢው ኮድ  በኮድ መሙያ ቦታው ላይ ተሞልቶ መምጣቱን ማየት ያሰፈልጋል፡፡ ከዚያም  ከኮድ 2–5 የተሞላላቸው በሙሉ ተከታዩን ዓምድ ዘለው ወደ ዓምድ 65 መሻገራቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

## **ዓምድ 64፡-** <u>የግል ሥራ /የራስን ድርጅት ለማቋቋም የገጠሞት/የሚገጥሞት ችግር አለ? ፣ ካለ ምንድነው?</u>

ይህ ዓምድ የሚሞላላቸው በዓምድ 63 ላይ ኮድ 1 የተሞላላቸው ማለትም የራሴን ድርጅት ማቋቋም እፈልጋለሁ ላሉ ግለሰቦች ብቻ ነው፡፡ የገጠሟቸው ወይም ሊገጥሟቸው ይችላሉ ተብሎ የሚገመቱ ችግሮች ከመጠይቁ ግርጌ ከኮድ 00–10  የተዘረዘሩ ስለሆነ ከነዚህ ምክንያቶች ውስጥ አንዱና ዋንኛው  ከላይ ባለው ክፍት ቦታ ላይ ተሞልቶ መምጣቱንና ተገቢው ኮድም ከሥር ባለው ካርድ ኮለም ውስጥ ተሞልቶ መምጣቱን ማገናዘብ ያሻል፡፡ ተሞልተው የመጡት ኮዶች ከ00–10 ካሉት ውጭ አለመሆኑን በጥንቃቄ ማየት ይገባል፡፡

## **ዓምድ 65፡** <u>ከዚህ በፊት በቅጥር ወይም በግል ሥራ ሠርተው ያውቃሉ ?</u>

ሥራ አጥ የሆኑ ግለሰቦች ከዚህ በፊት በቅጥር ወይም በግል ሥራ ሠርተው ያወቁ እንደሆነ በዚህዓምድ ይጠየቃሉ፡፡  ከዚህ በፊት በቅጥር  ሥራ ተሠማርተው ለሚያውቁ አዎን በቅጥር ኮድ 2፣ አዎን ለቤተሰብ ኮድ 3 ወይም አዎን በግል ሥራ ኮድ 4፣ በቅጥር ወይም በግል ሥራ ተሠማርተው ለማያውቁ ደግሞ የለም የሚለው ኮድ 1 ተሞልተው መምጣት አለባቸው፡፡ ከኮድ 1–4 ውጪ ተሞልቶ መምጣት የለበትም፡፡

## **ዓምድ 66፡-** <u>ለምን ያህል ወራት ያለ ሥራ ቆይተዋል?/በወራት ይገለፅ/</u>

በዚህ ዓምድ ሥራ አጥ የሆኑ ግለሰቦች በሙሉ ለምን ያህል ወራት ያለ ሥራ እንደቆዩ የሚጠየቁበት ሲሆን መረጃው በሙሉ ወራት ተሞልቶ መምጣቱን ማየት ተገቢ ነው፡፡ በካርድ ኮለሙ የተሞላው ቁጥር ከ97 በላይ ከሆነ ተሠርዞ ኮድ «97» ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በመጀመሪያው ንዑስ ዓምድ ምንም ሳይሞላ በሁለተኛው ንዑስ ዓምድ ብቻ ተሞልቶ ከመጣ የመጀመሪያው ንዑስ ዓምድ ላይ 0 መፃፍ ያስፈልጋል፡፡

## **ዓምድ 66A** <u>ራስዎን በምን ገቢ ያስተዳድራሉ?</u>

ይህ ዓምድ መልስ ሰጪዎች በተለይም ስራ ለመስራት ዝግጁ የሆኑ ሰዎች /ስራ አጦች/ ለረጅም ጊዜ ስራ ሳይሰሩ በማቆዩበት ጊዜ በምን መልኩ እራሳቸውን እንደሚያስተዳድሩ ለማወቅ ተጠይቋል። በዚህም ይረዳ ዘንድ አራት አማራጮች የተሰጠ ሲሆን፣ ከተጠቀሱት ውጭ ከሆነ ደግሞ ኮድ 5 ተሰጥቶት በፊደል ተፅፏል። እዚህ ላይ በፊደል የተፃፈው ከኮድ 1-4 ጋር ተመሳሳይነት ካለው በዚሁ ኮድ የሚካተት ይሆናል። ከነዚህ ኮዶች ውጭ ከሆነ ግን ስህተቱ ይስተካከላል

# ክፍል 5 : ያለፉት 12 ወራት የሥራ ሁኔታ

**ዓምድ 67:-** <u>ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን በምርታማ ሥራ ማለትም ተቀጥረው በክፍያ ወይም ትርፍ ለማግኘት ወይም ለቤተሰብዎ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርተው ነበር? ወይም ምርታማ ሥራ ለመሥራት ዝግጁ ነበረ?</u>

ለዚህ ጥያቄ እንደ አማራጭ የተሰጡት መልሶች "አዎን" እና "የለም" ሲሆኑ በዚህ መሠረት በዓምዱ ስር ስራ ሠርተወ ለነበሩ የሠሩት የሥራ ዝርዝር ወይም ዝግጁ ለነበሩ ይኸው ቃል (ዝግጁ ነበሩ) ከተፃፈ በካርድ ኮለሙ ኮድ 1 መፃፉን ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሁሉ ከተረጋገጠ በኋላ " የለም" ብለው ኮድ 2 የተሞላላቸው ቀጣዩን ዓምድ 68 ና 69 ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 70 መተላለፋቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል፡፡

**ዓምድ 68:** <u>ባለፉት 12 ወራት ለስንት ሳምንታት በሥራ ላይ ነበሩ ?</u>

ይህ ጥያቄ ተጠያቂዎች ባለፉት 12 ወራት ምን ያህል ሳምንታት በሥራ ላይ ምን ያህል ደግሞ ሥራ አጥ እንደነበሩ ለማወቅ በወራት ተከፋፍሎ ተጠይቋል፡፡ ስለሆነም በእያንዳንዱ ወር አንፃር "ሥራ ላይ" የነበሩበት ጊዜ ተጠይቆላቸው በዚህ ዓምድ ተሞልቷል፡፡ እናም ይህ ዓምድ እና ቀጣይ ሁለት ዓምዶች ላይ የተሞላው የሳምንታት ብዛት ተደምረው ከ49 የማይበልጡ/የማያንሱ መሆናቸው መጣራት አለበት፡፡

**ዓምድ 69:** <u>ባለፉት 12 ወራት ለስንት ሣምንታት ሥራ አጥ ነበሩ?</u>

በዚህ ዓምድ ተጠያቂዎች ለምን ያህል ሳምንታት ያለሥራ ሆነው ስራ ለመስራት ዝግጁ እንደነበሩ ተጠይቀዋል፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በዓምድ 67 ላይ ኮድ 1 የተሞላላቸው መሆኑን ማጣራት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በዓምድ 66 ከተሞላው የወራት ጊዜ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማየት ያሻል፡፡ <u>ለምሳሌ</u> በዓምድ 66 ላይ አንድ ግለሰብ ለ12 ወራት ያህል ያለስራ እንደቆየ የተሞላለት ከሆነ በዚህም ዓምድ ላይ የግድ 49 ሳምንታት መሞላት ይገባዋል፡፡ ካልሆነ ግን ስህተት ስለሆነ ተጨማሪ ማነፃፀር የሚያስፈልጋቸውን ዓምዶች በማየት ማረም ስለሚገባ ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን መፍትሔ መሻት ይገባል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ በዓምድ 67 ኮድ 2 ተሞልቶ በዓምድ 70 ደግሞ 49 የተሞላ ከሆነ ይህ ዓምድ በ --- /ሠረዝ የሚታለፉ ይሆናል፡፡

**ዓምድ 70:- <u>ባለፉት 12 ወራት ለስንት ሳምንታት ሥራ ለመሥራት አልቻሉም /ዝግጁ አልነበሩም?</u>**

ግለሰቦች ለዚህ ጥያቄ የመለሱት የሳምንታት ብዛት በዓምድ 70 እና 71 ከተሞላው ጋር ተደምሮ 49 መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ይህ ሆኖ ካልተገኘ ከሶስቱ ዓምዶች በአንዱ ብቻ ችግሩ ተከስቶ ሊሆን ስለሚችል ሌሎች ዓምዶች ጋር በማዛመድ ለማረም የሚቻል ከሆነ ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን ለማየት መሞከር ያስፈልጋል::

**ዓምድ 71 <u>በዚህ ዓምድ በዓምድ 68 እና 69 ባለፉት 12 ወራት በስራ ላይ እና ስራ አጥ ሆነው ያሳለፉበት ሳምንታት መረጃ ሰብሳቢው በመደመር ይመዘገባል</u>**

ይህ ዓምድ መረጃ ሰጪዎች ተጠይቀው የተሞላ ሳይሆን መረጃ ሰብሳቢው/ዋ ዓምድ 68 እና ዓምድ 69 የተሞላውን በመደመር ነው:: እዚህ ላይ ዓምድ 68 እና ዓምድ 69 በሰረዝ የታለፈ ቢሆንም በዚህ ዓምድ 00 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በሌላ አንፃር መረጃ ሰብሳቢዎች በዓምድ 70 ላይ የተሞላውንም የሳምንታት ብዛት ጭምር ደምረውት ሊሆን ስለሚችል ይህ አለመሆኑ ማረጋገጥ ይኖርበታል::

**ዓምድ 72:- <u>መረጃ ሰብሳቢ በዓምድ 71 ያለውን ጠቅላላ የሳምንታት ድምር በማየት ማረጋገጥ</u>**

በዚህ ዓምድ ላይ መረጃ ሰብሳቢው በዓምድ 71 የተሞላውን የሳምንታት ብዛት በማየት ያረጋገጠ ሲሆን፣ በዓምዱ /71/ የተሞላው 25 ሳምንታትና በላይ ከሆነ ኮድ 1 እና ከ25 ሳምንታት በታች ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 የተሞላ መሆኑን ማየት ያሻል::

**ዓምድ 73 <u>ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ሥራ ያልሰሩበት ወይንም ለመስራት ዝግጁ ያልነበሩበት ምክንያት ምንድን ነበር ?</u>**

ይህ ዓምድ ለመልስ ሰጪዎች ስራ ያልሰሩበትን ምክንያት ከተሰጡት አማራጮች ከ1-8 የመለሱ ሲሆን ከነዚህ ቁጥሮች/ኮዶች/ ውጭ ሌላ ከተሞላ መስተካከል ያስፈልገዋል:: በመሆኑም ሥራ ያልሠሩበት ዋነኛ ምክንያት በዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ ተገልጾ ተገቢው ኮድ ደግሞ ከስር ባለው ካርድ ኮለም ተሞልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ይገባል:: በተጨማሪም በዓምድ 72 ኮድ "2" እና በዓምድ 71 ከ25 ሳምንታት በታች የተሞላላቸው ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጠታቸው ይረጋገጣል::

**ዓምድ 74:- <u>የዋነኛ ሥራዎ የቅጥር (Employment Status) ሁኔታ ምንድነው ?</u>**

ምንም እንኳን ለአምድ 71 ኮድ 1 የተሞላላቸው ወደዚህ አምድ ቢሸገሩም ይህ አምድ ጥያቄ መጠየቅ ያለበት ለአምድ 68 1 ሳምንትና በላይ ለተሞላላቸው ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ለዓምዱ የተሰጠው ክፍት ቦታ ተሞልቶ የመጣው የቅጥር ሁኔታ ከሥር በካርድ ኮለሙ ከተሞላው ኮድ ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም ከጥያቄው ሥር የተዘረዘሩት 12 አማራጭ መልሶች ከኮድ 01-12 ብቻ ስለሆኑ ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ ሳይሞላ መምጣቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የአማራጭ መልሶች ዝርዝር መጠይቁ ላይ ከጥያቄው ሥር ቀርበዋል::

**ዓምድ 75:- <u>ዋነኛ ሥራዎ ምንድን ነው?</u>**

በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ለነበሩና ሥራ ኖሯቸው ነገር ግን በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ያልነበሩ ግለሰቦች (በዓምድ 34 ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው) በዚህ ዓምድ የዋነኛ ሥራቸው ዓይነት ተሞልቶ መጥቷል፡፡ ለዚህ ዋነኛ የሥራ ዓይነት ተገቢ የሆነው የመለያ ኮድ "የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ምደባና ኮድ ዝርዝር" ተብሎ ከተዘጋጀው መጽሐፍ በመውሰድ ኮዱ የተሞላ ቢሆንም የኤዲተሮች ዋና ሥራ የሚሆነው የኮዱን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ነው፡፡ የዋነኛ የሥራ ዓይነት ከኮድ ዝርዝር መጽሐፍ ውስጥ መጣጣም ካልቻለ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት ቢቻል ተቀራራቢ የሆነውን የሥራ ዓይነት ኮድ መሙላት ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በመስክ የተሞላው የሥራ ዓይነት ግልፅና በቀላሉ የማይነበብ ለመረዳትም አስቸጋሪ ከሆነ ኢዲተሩ በእርጋታና በትዕግስት መረጃ ሰብሳቢው የሞላውን ማጣራት ይኖርበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሥራ ዓይነት ኮድ ዝርዝሩ ጋር ለማገናኘት ሲሞክር በቅድሚያ የተጠቀሰው የሥራ ዓይነት በየትኛው ዋና ክፍል እንደሆነ መለየት ከዚያም በዋና ክፍሉ ሥር ከተዘረዘሩት የሥራ ዓይነቶች ለየትኛው እንደሚቀርብ አመዛዝኖ ኮድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሆኑም ለመወሰን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በመጠራጠር ኮድ ከማድረግ መቆጠብና ተቆጣጣሪውን በማማከር ትክክለኛውን ኮድ መስጠት ይገባል፡፡ ስለዚህ በኮድ ዝርዝሩ ከተሰጠው የማይጣጣም ሆኖ ከተገኘ ከተቆጣጣሪውና ከአሰሪው ክፍል ጋር ተነጋግሮ አዲስ ኮድ መስጠት ሊያስፈልግ ይችላል፡፡

**ዓምድ 76፡-** <u>ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ከግብርና ውጭ የሆነ ሥራ ሠርቷል?</u>

በግብርና እንደሚሰሩ የመለሱ ሰዎች በዓምድ 75 ከኮድ 1-3 የተሞላላቸው ሲሆን፣ በዚህ ዓምድ ደግሞ ከዚሁ የግብርና ስራቸው ውጭ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ተስማርተው እንደ ነበርና እንዳልነበር ተጠይቀዋል፡፡ ስለሆነም ተሠማርተው ከነበረ ኮድ 1 ካልነበረ ደግሞ ኮድ 2 ተሞልቷል፡፡ ከነዚህ ኮድ ውጭ ያለመሞላቱን ማየት ያስፈልጋል፡፡

**ዓምድ 77፡-** <u>የተጨማሪ ሥራዎ አይነት ምንድነው?</u>

በዓምድ 76 ላይ ከግብርና ውጭ የሆነ ተጨማሪ ስራ ሠራን ያሉ የግብርና ተዳዳሪዎች በምን ዓይነት ስራ ላይ ይህንን ተጨማሪ ስራ እንደሠሩ ተጠይቀዋል፡፡ ለዚህም መልስ ይሆን ዘንድ 16 ኮዶች በመጠይቁ የሽፋን ገፅ ላይ ተዘርዝረዋል፡፡ ስለሆነም ከተሰጡት ከነዚህ ዝርዝሮች ውጭ ኮድ ያለመስጠቱን ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡

**ዓምድ 78 ፡-** <u>ባለፉት 12 ወራት በካሽ ካገኙት ከጠቅላላ ገቢ ውስጥ ከግብርና ውጭ ሠርተው ያገኙት ድርሻ ምን ያህሉ ነው? /በመቶኛ ይገለጽ፡፡</u>

ይህም ዓምድ ከቀዳሚው ጥያቄ ጋር ተያያዥ ሲሆን፣ ለዚህ ጥያቄ ግለሰቦች በተጠቀሱት 12 ወራት ካገኙት አጠቃላይ ገቢያቸው ምን ያህለ ድርሻ/ Proportion/ ከግብርና ውጭ የተገኘ እንደሆነ ተሰልቶ ተቀምጧል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ድርሻውን ለማስላት አስቸጋሪ ሆነው የተገኙ ሁኔታዎች በተለያዩ ኮዶች የተሰየሙ ሲሆን፣ እነዚህም '95' ከፍተኛው የድርሻ መጠን ሲሆን፣ 96፣ ደግሞ መልስ ሰጪዎች የግብርናውን ምርት በካሽ ሳይቀይሩት ከግብርና ውጭ የሆነውን በካሽ ካገኙ የተሰጠ ኮድ ነው፡፡ እንዲሁም ኮድ 97 የግብርናው ገቢ/ካሽ ታውቆ የተጨማሪው ስራ በዓይነት ከሆነና በገንዘብ ካልተቀየሩ ሌላ ደግሞ ኮድ 98 ሲሆን፣ ይኸውም ገቢ ከምግብ በስራ የተገኘን ገቢ ለማመልከት ነው፡፡ ስለሆነም፣ በዚህ አምድ ከ00 እስከ 98 ድረስ ቁጥሮች ሊሞሉ የሚችል ሲሆን ከዚህ ውጭ ያለመሞላቱን ማየት ያሻል፡፡